<u>ቀን 30/11/99 ዓ.ም.</u>

**በአውሮፓ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ**
**የድጋፍ ሰጭ ምክር ቤት (Council) ሊቀመንበር**
**ስዊዘርላንድ**

**ጉዳዩ፡- የስራ ጉዞ ልዑካንንና የአቀባበል ዝግጅት ኮሚቴ አባላትን ስለማሳወቅ**

ከሁሉ አስቀድመን እኛ ከእስር የተፈታን የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አመራሮች፤ በአውሮፓ የምትገኙ የድርጅቱ አባላት፣ደጋፊዎችና የኢትዮጵያ ወዳጆች ከሌሎች በውጭና በአገር ውስጥ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን ከእስር እንድንፈታ ላደረጋችሁት ብርቱ ትግል በእስር በነበርንበት ጊዜ ይሰጠን የነበረውን የሞራል ብርታትና የህሊና እረፍት እያስታወስን ደግሞም ከተፈታን በኋላ ስለሰጣችሁን አስደናቂ ፍቅርና ስላሳያችሁን አክብሮት በድጋሚ ልባዊ ምስጋናችንን በኢትዮጵያ ህዝብ ስም እናቀርባለን፡፡

ከእስር የተፈታን የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አመራሮች ሐምሌ 27 ቀን 1999 ዓ.ም ባደረግነው ልዩ ስብሰባ ወደ ተለያዩ አህጉራት ስለሚደረገው የስራ ጉዞ፣ስለሚካተቱት የልዑካን ቡድን አባላትና የአቀባበል ዝግጅት ኮሚቴ አወቃቀርን በተመለከተና በሌሎችም ተያያዥነት ባላቸው ዝርዝር ጉዳዮች ላይ በሰፊው መክሮ የሚከተለውን ውሳኔ አስተላልፈናል፡፡

1. ወደ አውሮፓ የሚላኩ የድርጅቱ የልዑካን ቡድን አባላትን በሚመለከት፡-

| | |
|---|---|
| 1ኛ. አቶ ሙሉነህ ኢዮኤል | የልዑካን ቡድኑ መሪ |
| 2ኛ. ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም | አባል |
| 3ኛ.አቶ አባይነህ ብርሃኑ | አባል |
| 4ኛ.አቶ ክፍሌ ጥግነህ | አባል |
| 5ኛ. አቶ አስቻለው ከተማ | አባል |

2. የልኡካን ቡድኑ ጉብኝቱን የሚያደርግበት ጊዜ እ.ኤ.አ ከነሐሴ 20/2007 በኋላ እንዲሆን፣

3. የልዑካን ቡድኑን ጉብኝት አስተባባሪ ኮሚቴ አባላትን በሚመለከት፡-
ስራውን በአውሮፓ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የድጋፍ ሰጭ ምክር ቤት (Council) እንዲያከናውን ወስነናል፡፡

ስለሆነም በአውሮፓ የምትገኙ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የድጋፍ ሰጪ ድርጅቶችና ሌሎች አካላት ይህንኑ በመገንዘብ ለካውንስሉ አስፈላጊውን የገንዘብ የሰው ኃይልና የሎጀስቲክ ድጋፍ እንድታደርጉላቸው እንጠይቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር!

አቶ ኃይሉ ሻውል
ፕሬዚደንት